# አዲስ

## “ እነሆ የቀድሞው ነገር ተፈፀመ ÷ አዲስ ነገርን እናገራለሁ ፤

ኢሳ 42 ÷ 9

እግዚአብሔር አዳዲስ ነገሮችን ማድረግ እንደሚወድ ያውቃሉ ?

**አዲስ ፍጥረት አደረገን :-**

“ ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ። ”   2ቆሮ 5 ÷ 17

**አዲስ መንገድ አሳየን :-**

“ እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በመረቀልን በአዲስና በህያው መንገድ
ወደ ቅድስት እንድንገባ ድፍረት አለን ”  ዕብ 10 ÷ 19

**አዲስ መንፈስ አዲስ ልብን ሰጠን :-**

“ አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ ፤ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ ። ”
ሕዝ 36 ÷ 26

**አዲስ ዕውቀትን ሰጠን :-**

“ እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል ። ”
ቆላ 3 ÷ 10

**አዲስ ምሳሌን ሰጠን :-**

“ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን ። ”
2ቆሮ 3 ÷ 18

**አዲስ ቅኔን ( መዝሙርን ) ሰጠን :-**

“ አዲስ ቅኔን ተቀኙለት ÷
በእልልታም መልካም ዝማሬ ዘምሩ ። ”   መዝ ( 33 ) ÷ 3

**አዲስ ምህረትን ሰጠን :-**

“ ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው ፤
ርኅራኄው አያልቅምና ።
ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው ፤ ታማኝነትህም ብዙ ነው ። ”
ሰቆ. ኤር 3 ÷ 22

አዲስ ነገር ከሚሰራው ጌታ ጋር አዲስ ሕይወት ጀምረዋል ?

# አንተ መላጣ ውጣ !

“ ከዚያም ወደ ቤቴል ወጣ ፤ በመንገድም ሲወጣ ብላቴኖች
ከከተማይቱ ወጥተው :- አንተ መላጣ ÷ ውጣ አንተ መላጣ ÷ ውጣ
ብለው አፌዙበት ። ”

2ነገ 2 ÷ 23

በቤቴል :- አዎን ! በቤቴል የእግዚአብሔር አገልጋይ ፤ እጥፍ መንፈስን የተቀበለው ተፌዘበት ፤ ተቀለደበት -------- በቤቴል ።

በአገልግሎቱ መጀመሪያ ኤልሳ ተቃዋሚዎች ተነሱበት ኤልሳ እጥፍ መንፈስን ተሞልቶ አገልግሎቱን እንደጀመረ ----- ተቃውሞ ምነው ?

እጥፍ ድርብ መንፈስ ፤ ቅባት ሲሰጠን ሰይጣን ዝም አይልምና ይነሳል ለውግያ የራሱን ወገን ያሰልፋል ፤ ቢቻለው ቅባታችንን ለማስጣል ይታገላል ። እጥፍ ቅባት ÷ እጥፍ ውግያን ይጠይቃልና ።

በቅባት ስትወጣ ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በእጥፍ በአንተ መስራት ሲጀምር ጠንቀቅ ነው ሰይጣንም ውጊያውን በእጥፍ ማድረጉ የማይቀር ነው ።

ውግያውም ከቤቴል ይጀምራል ።

አይመስሎትም ?

# ምን ያህል ?

" በዚህ ሸለቆ ሁሉ ጉድጓድ ቆፍሩ ፤
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፡-
ነፋስ አታዩም ፥ ዝናብም አታዩም ፥
ይህ ሸለቆ ግን ውሃ ይሞላል ። "

2 ነገ 3 ፥ 17

በኤዶምያስ ምድረ በዳ ሰባት ቀን ጉዞ ፤ ፍርሃት ጭንቀት የተሞላ ጉዞ ። ወዮ ! እግዚአብሔር በምድረ በዳ ያጠፋን ዘንድ ወደዚህ መራን --- ወዮ ! ያሰኝ ጉዞ ፤ የእንባ ጉዞ ፤ ለውግያ ጉዞ -------- የስጋት ጉዞ ።

መውጪያ ቀዳዳ ሲጠፋ ጌታን ብቻ የምንታመንበት ጉዞ
የኤልያስ አምላክ እግዚአብሔር የት አለ ? ያሰኝ ጉዞ ፤ ---- ሃይለኛ ጉዞ ።

ፊታችንን ወደ ጌታ በምንመልስበት ሃይለኛ ወቅት እግዚአብሔር ራሱን ገልፆ " በዚህ በረሃማ ሸለቆ ጉድጓድ ቆፍሩ " ይላል

በዚህ ሃይለኛ ወቅት ፤ ለመታመን በሚያስቸግር ሁኔታ
እግዚአብሔርነቴን አሳያለሁና ጉድጓድ ቆፍሩ ይላል -- እግዚአብሔር

በረሃ ነው ፡- ነፋስ አታዩም ፤ ዝናብም አታዩም ነገር ግን የቆፈራችሁት ጉድጓድ ውሃ ይሞላል ።
አይታመንም ግን ይሆናል ። ይላል እ-ግ-ዚ-አ-ብ-ሔ-ር

ይህ ትዕዛዝ ለእርስዎ ቢሆን ምን ያህል ጥልቀት ያለው ጉድጓድ ይቆፍራሉ ?

ልብ ይበሉ ! በቆፈሩት ልክ ነውና ውሃው የሚሞላው ። ትልቅ ፤ ጥልቅ ጉድጓድ ብዙና የተትረፈረፈ ውሃ ይይዛል ። አይመስሎትም ?

# ቅጥረኛ እረኛ

" ከእኔ ዘንድ ተቀመጥ ፥ አባትና ካህንም ሁነኝ ፤ እኔም ልብሶችንና ምግብህን ፥ በእየዓመቱም አሥር ብር እሰጥሃለሁ አለው ። ሌዋዊውም ገባ ። ሌዋዊውም ከሰውየው ጋር ለመቀመጥ ፈቀደ ። "

መሳ 17 ፥ 7 - 13

በቤተ ልሔም ፤ በይሁዳ ይቀመጥ የነበረው ሌዋዊ ሄደ ወጣ ፤ ቤተ ልሔምን ለቀቀ ። ከቤተ ልሔም የተሻለ ስፍራ ፍለጋ ፤ መቀመጫ ፤ ሄደ ፤ ወደ ሚካ ቤት ደረሰ ፥

ቤተ ልሔማዊ ካህን መሆኑን ያወቀ ሚካ ቀጠረው የራሱ አደረገው በገንዘቡ ወሰደው ።

ፍላጎቱ ተሳካ ፤ ሰመረለት ፤ ስፍራ ተገኘለት ካህኑ ።
ሚካም ሃሳቡ ሆነለት ፤ ተሳካለት ካህን ቤቱ መጣለት ለአምላክ ሊያጥን ፤ ሊሰዋለት ።

ጊዜ ሄደ ፤ ሮጠ ፤ ሚካና ካህኑ ተስማሙ ።

ግን አንድ ቀን ፤ አንድ ወቅት የተሻለ በረከት ፤ የተሻለ ክፍያ ሲመጣ ( መሳ 18 ፥ 19-20 ) ልብ ደስ የሚያሰኝ ፤ የስጋን ፍላጎት የሚያረካ ፤ ሄደ ትቶ ሚካን ፥ ቅጥረኛ እረኛ ፤

ለበጎች ልቡን ያልሰጠ ፤ ለበጎች ጥሪ የሌለው ፤ ስም ብቻ የተሸከመ እረኛ ፤ ቅጥረኛ እረኛ ።

ነፍሱን ለበጎቹ ያላኖረ እረኛ ( ዮሃ 10 ፥ 11- 13)

የእርሶስ እረኝነት ?

በቅጥር ነው ? --------- ወይስ በጥሪ ነው ?

------- ጠንቀቅ ነው ?

## በደለኛ

" እኛም ዝም ብለናል ። "

2 ነገ 7 ፥ 9

ሕዝብ ተርቧል ፤ እናት በልጅዋ ላይ ጨክናለች ፤
እኛ ያገኘነውን ቢያገኙ ፤ እኛ የበላነውን ቢበሉ ፤ ያየነውን ቢያዩ ፤ ነገሮች ይለወጣሉ ።

ግን ! ------ እኛ እኮ ለምፃሞች ነን ! የምስራችን መናገር የማያምርብን የማንሰማ ፤ ግን ! እኛ እኮ ሃጢያተኞች ነን ከከተማ ውጭ የምንቀመጥ ፤

እኛ እኮ ! ----- እኔ እኮ ! ----
ብዙ ምክንያት ፤ ብዙ ነገር መደርደር ----
በተባረክነው በረከት ፥ ሌላውን ሳለ መባረክ ። ያገኘነውን ሌላው እንዳያገኝ ።

" እስኪነጋ ድረስ ብንቆይ በደለኞች እንሆናለን " አሉ እነዚህ ለምፃሞች
ሄዱ ! ሳይለፉ ያገኙትን ለማካፈል ሮጡ ፤ ገሰገሱ ።

እርስዎ እንዲሁ በነፃ ያገኙት የዘላለም ሕይወት በረሃብ ሳለ ሕዝብ ፈውስ መሆኑን አውቀዋል ?

ኢየሱስን ያካፍላሉ ? ያሳያሉ ?
ለምን እስኪነጋ ይቆያሉ ? ዝም ይላሉ ? በደለኛ ይሆናሉ !

## ለውጥ

" መባቻ ወይም ሰንበት ያይደለ ። ዛሬ ለምን ትሄጂበታለሽ ? "

2 ነገ 4 ፥ 23

ደርሶ ያስቸግረናል ፤ እንቢ ይለናል ።
አይሆንልንም ፤ አይሰምርልንም ፤ አይሳካልንም ።
አልፈን ለመውጣት ጥረቱም ሃይለኛ ነውና አንሻውም ፤ አንፈልገውም ።

የለመድነውን ፤ የተለማመድነውን አልፈን መሄድ ፥ መቀየር ያስቸግረናል አዲስን ነገር ማድረግ ፤ መለማመድ ፥ ያለውን ያበላሽ ይመስል አንደፍረውም ደርሶ እንሰጋለን ።

የሱነማይቱ ባለቤት በመባቻ ወይም በሰንበት ነው መንፈሳዊ ነገር የሚደረገው ፤ በመባቻ ወይም በሰንበት ነው ነቢይ የሚታየው ዛሬ ለምን ትሄጂበታለሽ አላት ።

ያለ መባቻ ፤ ያለሰንበት መደረግ አይገባው ይመስል ፥ ከተለመደው ውጭ አይደረግ ይመስል ፤ ካደረግነው ውጭ አናደርገው ይመስል አዲስ ነገር ያስፈራናል ።

ለውጥን ፈርተን ሳንለወጥ ፤ አዲስን ፈርተን ሳንታደስ ስንት ዘመን ?

# አንድ ብቻ ?

" ሶስት ቀንም ፈልገው አላገኙትም "

2 ነገ 2 ፥ 17

ሄዱ ! ሶስት ቀን ሙሉ ተንከራተው ተመለሱ ፡፡
ኤልያስ የለም ፤ ጌታ ወስዶታልና አልተገኘም ፡፡
አትሂዱ ተብለዋል ተመክረዋል ---- አልሰሙም ፡፡

ምነው ቀድሞ አልተከተሉት ? ምነው ቀድሞ አላገለገሉት ?
<u>ምነው ቅባቱን ሳይሆን ባለቅባቱን ወደዱ ፤ ፈለጉ</u> ? ምነው ?

ለምን እጥፉን መንፈስ አልጠየቁም ? አልፈለጉም ? --- ምነው ?

ለምን ከዮርዳኖስ ማዶ ቆመው ቀሩ
ምነው ! አብረው አልተሻገሩ ? ከእጥፉ መንፈስ ተካፋይ አልሆኑ ? ምነው ?

ምነው ! ዛሬ ከበባ ? ምነው ዛሬ ፍለጋ ? ------- ድካም ----- መና

ምነው ! ከሃምሳ ሰው አንድ ብቻ
ለመቀባት የሚፈልግ የተጠማ ?

# ምነው ?

" ከብዙ ቀንም በኋላ በምድር ላይ ዝናብ አልነበረምና
<u>ወንዙ ደረቀ</u> ፡፡ "

1ኛ ነገ 17 ፥ 2 - 7

አዎን !

የእግዚአብሔር ቃል ነው የመጣለት ፡፡
በኮራት ፈፋ ውስጥ ተሸሸግ ፤ ከወንዙ ትጠጣለህ
ቁራዎችም በዚያ ይመግቡህ ዘንድ አዝዣለሁ ያለው
እግዚአብሔር ነው ፡፡

ኤልያስም እንደ እግዚአብሔር ቃል አደረገ ፡፡ ሄደ ፤
ቁራዎቹም በየጥዋቱና በየማታው እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር ፡፡
ከወንዙም ይጠጣ ነበር ፡፡

እግዚአብሔር ለአገልጋዩ ልዩ ጥንቃቄን አደረገ ፡፡

ታዲያ ! <u>ምነው ወንዙ ደረቀ</u> ?
ምነው ውሃው ቆመ ? ---- እግዚአብሔር አዞት ከሄደ ?

ባይደርቅ ወንዙ መች ይሄድ ነበር ሰረፕታ ፡፡
ባይሄድ ሰረፕታ መች ትድን ነበር ባልቴትዋ ፡፡
መች ይጨምር ነበር እምነቱ ፡፡

ቢደርቅ ወንዙ ለጥቅማችን ነው ፤ ለእድገታችን ፡፡
እኛ ግን በጌታ እንበርታ ፤ እንሁድ ፤ እንኑር ፡፡

## ጥቂት ውሃ

" ተነስቶም ወደ ሰረፕታ ሄደ ፤ ወደ ከተማይቱም በር በደረሰ ጊዜ አንዲት ባልቴት በዚያ እንጨት ትለቅም ነበር ፤ እርሱም ጠርቶ ፦ የምጠጣው ጥቂት ውኃ በዕቃ ታመጭልኝ ዘንድ እለምንሻለሁ አላት ። "

1 ነገ 17 ፥ 8-12

አስደናቂ የሆነች ሴት ነች ፤ እፍኝ ዱቄት ፤ ጥቂት ዘይት ብቻ ያላት ፥ ነገር ግን ለዛ ላላት እፍኝ ዱቄትና ጥቂት ዘይት ማብሰያ እንጨት ለመለቃቀም ፤ ለመስራት ጉልበት ፤ ሃይልና ፍላጎት የነበራት አስደናቂ የሆነች ባልቴት ሴት ነች ።

ለየት ያለች ባልቴት ሴት ነች ፤ በፀሃይ ንዳድ ክስል ያለ ፊት ይዞ ፤ አልፎ ወደ እርስዋ ለመጣው ሰው ምንም እንኳ የሰማይ በሮች ተዘግተው ውሃ ባይኖርም ያላትን ለማካፈል ችግር የሌለባት አስገራሚ ሴት ነች ይህች ባልቴት ።

በችግርዋ ፤ በመከራዋ ወቅት ፤ በባዶነትዋ በጨለማዋ ሰዐት እርስዋ ልትለምን በሚገባበት ወቅት ከራስዋ በፊት ለሌሎች ቅድሚያን በመስጠት ያገለገለች ግሩም ሴት ነች ።

ያላትን ፥ አለኝ ማለት የምታውቅ ሴት ፤ ትንሽ ነውና አይጠቅምም ከማለት ይልቅ እርሱኑ ለማካፈል የወደደች ሴት ፤ ታላቅ ሴት ።

ወደ ራስዋ ችግር ብቻ እየተመለከተች ከማማረር ይልቅ ዓይኖችዋን ከፍታ ከእርስዋ የበለጠ ከንፈሩ የደረቀውን ፤ የደቀቀውን ፤ የተጎዳውን ወገን ማየትና ማገልገል የምታውቅ ውብ እህት ነች ይህች ሴት ።

አይናችንን ከከፈትን ፤ ከወደድን ----- እርግጥ ነው ወደኛ የሚመጣ ከንፈሩ የደረቁበት ሰው እናያለን ። ---------- ---------------- ሁል ጊዜ በዙሪያችን ናቸውና !!

## ወዴት ነው !

### " የኤልያስ አምላክ እግዚአብሔር ወዴት ነው ? "

2 ነገ 2 ፥ 14

መንፈሳዊ አባቱ ነው ።
እጥፍ መንፈሱን የሰጠው የቅርብ አስተማሪው ።
የአብርሃም ፤ የይስሃቅና የያዕቆብ አምላክ የሆነውን ሕያው
እግዚአብሔርን ማምለክ ምን መሆኑን ያሳየው መሪውም ነው ።

ግና ! የኤልያስ አምላክ እግዚአብሔር ወዴት ነው አለ ።

ኤልያስ ወዴት ነህ ? መተላለፊያ መንገድ ሳጣ
ኤልያስ ወዴት ነህ ? ብቻዬን ስቀር
ወዴት ነህ ኤልያስ ? ዮርዳኖስ በፊቴ ሲቆም

አ ---- ላ --- ለ --- ም !

የኤልያስ አምላክ እግዚአብሔር ወዴት ነው ?
አዎን ! ኤልያስ አምላኩን እግዚአብሔርን ለኤልሳ ገለፀለት እንጂ አደራረጉን ብቻ ገልፆለት አልሄደም ።

መዝ ( 103 ) ፥ 7 " ለሙሴ መንገዱን አስታወቀ ፤
ለእስራኤል ልጆችም አደራረጉን ። "

በማለት የእስራኤል ልጆች የእግዚአብሔርን አደራረግ ብቻ እንጂ እግዚአብሔርን በግል ሳያውቁት እንደቀሩ የፃፈልን ለትምሕርታችን ነውና ---- እ ----ር ---- ሶ ---- ስ ?

እግዚአብሔር ወዴት ነው ? ማለት የሚያስችል በእርግጥ የተገለፀ ዕውቀት አለዎትን ?

# ሕይወት አልባው ሙቀት

“ኤልሳም ወደ ቤት በገባ ጊዜ እነሆ ሕፃኑ ሞቶ በአልገም ላይተጋድሞ ነበር ፡፡ ገብቶም በሩን ከሁለቱ በኋላ ዘጋ ወደ እግዚአብሔርም ፀለየ ፡፡ መጥቶም በሕፃኑ ላይ ተኛ ፤ አፉንም በአፉ ፥ ዐይኑንም በዐይኑ ፥ እጁንም በእጁ ላይ አድርጎ ተጋደመበት ፤ የሕፃኑም ገላ ሞቀ ፡፡ ”

2 ነገ 4 ፥ 32-34

እንጀራ ይበላ ዘንድ ግድ ያለችው ሴት ፤ ስፍራን ያዘጋጀችለት ሴት ትንከባከበው የነበረች ሴት ፤ ቸርነትን በማግኘት ልጅን በስተርጅና ያገኘች ሴት ፤ ያ የተወደደ ልጅዋ ከጌታ የተሰጠ አንድያ ልጅዋ ሞተ ፡፡

ሄደች ! ቀርሜሎን ተራራ ድረስ ፤ ኤልሳን ፍለጋ ተጓዘች ----- ኤልሳ ወደ ሱነማይቱ ቤት በመምጣት ልጅዋን ከሞት ያስነሳ ዘንድ ተማፀነች ለመነች ፡፡

ኤልሳም በሱነማይቱ ቤት በመምጣት በህፃኑ ገላ ላይ ተጋደመበት ፤ ወደ እግዚአብሔር ፀለየ ፤ እንደገና ተጋደመበት መፅሃፍ ቅዱሳችን እንደሚል የሕፃኑ ገላ ሞቀ ------- ገላው ከሞቀ ምነው ደግሞ ተጋደመበት ?

“ የሞቀ ገላ ሁሉ በሕይወት ያለ ገላ አይደለምና ” ጠንቀቅ ነው ! ብዙ የሞቁ ፤ ነገር ግን ሕይወት የሌላቸው ወንድሞችና እህቶች በዙሪያችን ሞልተዋልና እጆቻችንን ልንዘረጋላቸው ፤ በዐይኖቻችን ልናያቸው ፤ በእጆቻችን ልንዳስሳቸው የተገባ ነው ፡፡

ልብ ይበሉ ----- “ የሞቀ ሁሉ በሕይወት ያለ አይደለምና ”

# “ በዚህ ለምን እንቀመጣለን ? ”

2 ነገ 7 ፥ 4

እስክንሞት ድረስ በዚህ ለምን እንቀመጣለን ?
ነገሮች እንደቀድሞው አይደሉም ?
የከተማው ሕዝብ እንኳን ለሰው የሚያተርፈው ለራሱም የለው ፤ የተራበ ነው ፡

ቀድሞ ከከተማው ውጭ ከሚጣል ምግብ ትርፍራፊ እንኖር ነበር ዛሬ ግን የሚመግበኝ ተርቧል ፡፡

አራት ለምፃም ሰዎች ፤ ከተማ መግባት ያልተፈቀደላቸው ፤ ሕዝብ መገናኘት የማይችሉ ፡፡ ------ የኛ መምህራን !

በዚህ ለምን እንቀመጣለን ? መጋቢው ከተራበ ፡፡
በዚህ ለምን እንቀመጣለን ? ባለምግቡ ምግብ ካጣ ፡፡

የራሳቸውን እርምጃ ወሰዱ ፤ ሄዱ ፤ ከመጠበቂያቸው ዘወር አሉ የተትረፈረፈንም ምግብ አገኙ ለሌላም ተረፉ ፡፡

መጋቢው ከተራበ ፥ የራሴን ምግብ ራሴው እቆፍራለሁ ፤
እሄዳለሁ
“ አጠናለሁ ” ቆፍራለሁ ----- ለሌላም እተርፋለሁ --------- አዎን !
በዚህ ለምን እቀመጣለሁ ?

የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ

ይወስዳቸዋል !

የእርሱ በግ ነዎት ?

# ከሜዳ

“ በምንቸቱ ውስጥ ሞት አለ ”

2 ነገ 4 ፥ 38 – 41

ባለ እጥፍ መንፈሱ ኤልሳ ተከበበ ፤ በነብያት ልጆች ጉባኤ ታጠረ ። ሰማያዊ ትምሕርትን ለመቅሰም ፤ የጌታን ሃሳብ ለመረዳትና እንደ ሃሳቡም ለመመላለስ መንፈሳዊ ትምሕርት ለመሞላት ።

ሰብስቦ ሲያስተምራቸው ፤ ሲገልፅላቸው ፤ መንፈሳዊ ዓይኖቻቸውን ሲያበራላቸው ከዋለ በኋላ ለስጋም የሚሆናቸውን ምግብ ለማዘጋጀት ምንቸቱ እንዲጣድ አዘዘ ።

ምንቸት ተጣደ ፥ አንዱም ሄደ ወጣ ፤ ወደ ሜዳ የሚቀቀል ፍለጋ --- ሰበሰበ --- አመጣ

ምግቡ ደርሶ ሲበላ ሞት በምንቸቱ ውስጥ ነበረና ሁሉም መመገብ አቃታቸው ---- ተፉት --

በአንዱ ሰው በኤልሳ ---- ሕይወት የሚገኝበት ትምሕርት
በአንዱ ሰው በሌላው ---- ሞት በሕብረት ውስጥ

ከሜዳ የተሰበሰበ ፤ የታጨደ ፤ የታፈሰ ----- ሕብረትን የሚገድል ምግብ መሰል ሞት ።

ተጠንቀቅ ! ምን እንደምታመጣ ለሕብረቱ
ተጠንቀቅ ! ይህ ሕብረት ጌታ የሞተለት ሕብረት ነውና ------- ተጠንቀቅ !

ከሜዳ የተሰበሰበውን ሳይሆን ፥ ከጌታ የተሰበሰበውን አምጣልንና መግበን --- ሕይወት እንዲሆንልን።

# እኔ

" ምን አድርጌልሃለሁ ! "

1ኛ ነገ 19 ፥ 20

ድንገት ደረሰና መጎናፀፊያውን በላዩ ጣለበት ፤
ኤልሳ !- የቀድሞው ኤልሳ መሆን አልቻለምና
በቅፅበት እግዚአብሔር ሳዘጋጀለት ግልጋሎት ሊወጣ ሲነሳ የመጨረሻ
ስንብትን ያደርግ ዘንድ ለመነ ።

እኔ ምን አድርጌልሃለሁ ? ለዚህ ግልጋሎት ጥሪን ያቀረበልህ
እግዚአብሔር እንጂ እኔ አይደለሁምና ነገሮችን ከኔ ጋር አታያይዛቸው

እኔ ምን አድርጌልሃለሁ ? አድርግ የተባልኩትን
አደረኩ እንጂ ---- እኔ ምን አድርጌልሃለሁ ?

ኤልያስ ፦ በማንኛውም መንገድ ክብርን ለእግዚአብሔር
እንጂ ለራሱ እንዳያደርግ ታላቅ ጥንቃቄን ያደርግ እንደነበር መገንዘብ
እንችላለን ።

እኔ እዚህ አድርሼው ---- የማያሰኝ ግልጋሎትን ወዳድ ነው ኤልያስ ።

እርሶስ ?

# ያስቀናል !

" ልጄን ትገድል ዘንድ ወደ እኔ መጥተሃልን "

1 ነገ 17 ፥ 17-18

አስደናቂ የሆነች ሴት ነች ይህች ባልቴት ሴት ።
ምን ትንሽ ቢሆን ያላት ዱቄትና ዘይት ዛሬም እንደወትሮዋ ትሰራለች ፤ እንጨት
ትለቅማለች ።

በተትረፈረፈ ጊዜ የምታደርገውን በጎደለ ጊዜም ማድረግን
የምታውቅ ሴት ነች ።

ኤልያስን ጌታ ልኮ ያን የመከራ ዘመን ማሳለፍዋ ተዓምር ቢሆንም
ልጅ የማግኘትዋ ግን እርስዋንም ያስደነቀ ድንቅ ነበር ።

ዱቄቱ ከማድጋ ፤ ዘይቱ ከማሰሮ ሳይጎድል የረሃቡን ዘመን
ብታሳልፍም
በዘይት ብትትረፈረፍም ፤ ከጌታ ዘንድ በሆነ ዘይት ያንን ዘመን ብታሳልፍም
ሞት ! አዎን ሞት ቤትዋ መጣ --------- ልጅዋን ወሰደባት ----- ልብዋን
ሰበረባት ሞት ።

አገልጋይ እኮ ነች ? ነቢይ የቀለበች ፤ ያስተናገደች
ጌታ በክፉ ዘመን የተጠቀመባት ። ምነው ? ሞት መጣባት ? ልጅዋን ወሰደባት ?
ነጠቃት ? ልብዋን ሰበረባት ?

ያስቀናል ! እያገለገሉ መሄድ ፤ መጠራት ፤ መወሰድ ------
ያስቀናል ! በጌታ መታወቅ ፤ ጌታን ማወቅ ------
ያስቀናል ! ከሚወዱት ጋር በገነት መሆን ፤ መለየት ------
ያስቀናል ! ሊገድለን ሳይሆን ሊያሳርፈን መምጣቱ -------

በአገልጋዩም ቤት ሞት አለ ዕንባ ፤ ለቅሶ ።

## ልጅሽን ስጭኝ

" ከዚህም በኋላ የባለቤቲቱ ልጅ ታመመ ፤
ትንፋሹም እስኪታጣ ድረስ ደዌው እጅግ ከባድ ነበር :: "

1ነገ 17 ÷ 19

ኤልያስ !
ይህ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው ::
አንቺ እንዲህ በመሆንሽ የሆነ ነው እንጂ ሌላ አይደለም ::
በማለት ሁኔታውን ከማብራራትና ምክንያት ከመስጠት ይልቅ
ልጅሽን ስጭኝ ! አላትና ወደ ሰገነቱ አገባው ወደ ውስጠኛው ክፍል

ይህ ክፍል ፤ ውስጠኛው ክፍል ፤ የፀሎት ክፍል
ህብረት ከጌታ ጋር የሚደረግበት ክፍል :: የአምላክ ፊት የሚሻትበት
ክፍል ::

ልጅሽን ስጭኝ !
ሃዘንሽን ስጪኝ !
የተበላሸው ትዳርሽን ስጪኝ !

የተሰበረ ልብህን ስጠኝ !
ያልተሳካ አገልግሎትህን ስጠኝ !
ያልሰመረ እቅድህን ስጠኝ !

አዎን !

የጌታ መንፈስ በእርሱ ላይ የሆነ ፤
ለድሆች ወንጌልን የሰበከ ፤ የተቀባ ፤
ለታሰሩት መፈታትን ፤ ለዕውሮች ማየትን ፤
የተጠቁትን ነፃ የሚያወጣ
የተወደደችውን የጌታን ዓመት ያበሰረን ጌታ

ልጅሽን ስጪኝ
ሃዘንሽን ስጪኝ
የተበላሸ ትዳርሽን ስጪኝ

የተሰበረ ልብህን ስጠኝ
ያልተሳካ አገልግሎትህን ስጠኝ
ያልሰመረ እቅድህን ስጠኝ ፤

ምን ትሻለህ ?
ሕይወት ያለው ፤ ወይስ -----------

## ስራ ! ለሰራተኛ

" ከዚያም ሄደ ÷ የሣፋጥንም ልጅ ኤልሳዕን በአሥራ ሁለት ጥማድ
በሬዎች ሲያርስ ÷ እርሱም ከአሥራ ሁለተኛው ጋር ሆኖ አገኘው :: "

1ነገ 19 ÷ 19

በኮሬብ ተራራ በጎቹን ሲያሰማራ ፤ በትጋቱ ወራት ጌታ ለሙሴ ተገለፀለትና ለበለጠ አገልግሎት ሾመው :: ዘፀ 3 ÷ 1- 12

ማቴዎስ :- በቀራጭ ጠረጴዛው በአገልግሎቱ ላይ እያለ ጌታ ለተሻለ አገልግሎት ጥሪ አደረገለት :: ሉቃ 5 ÷ 27-28

ጴጥሮስ ዮሃንስንና ያዕቆብን አሳ በማጥመድ ሲተጉ አግኝቶ ሰውን ማጥመድ ያለማምዳቸው ዘንድ ከአገልግሎት ሁሉ ወደ በለጠና ወደ ተሻለ አገልግሎት ጠራቸው :: ማቴ 4 ÷ 18 - 22

ሌሎችም አያሌ ወንድሞችና እህቶች ለጌታ አገልግሎት ሲጠሩ በታላቅ ስራ ላይ ሆነው በታማኝነት በማገልገል ላይ እንዳሉ ነበር ለተሻለ አገልግሎት የተሻለ ጥሪ የተደረገላቸው

ኤልሳም በኤልያስ ለታላቁ ተልዕኮ ሲጠራ ከሞያተኞቹ ጋር በግብርና ስራ ላይ እያለ ነበር እንጂ ቁጭ ብሎ የጌታን ቅባት በመጠባበቅ ላይ አልነበረም ::

ምን እንማራለን ከዚህ ? ------------- አደራ ስራ ፊት ሆነን እንዳንቀመጥ

በስራ ላሉ ነው የተሻለ ስራ ! አይመስሎትም ?

# እኛው እናምጣ ፤ እኛው እንስራ

“ የነቢያትም ልጆች ኤልሳዕን ፡- እነሆ በፊትህ የምንቀመጥበት ስፍራ ጠብቦናል። ወደ ዮርዳኖስም እንሂድ ፥ ከእኛም እያንዳንዱ ከዚያ ምሰሶ ያምጣ ፥ የምንቀመጥበትንም ስፍራ በዚያ እንስራ አሉት ። ”

2 ነገ 6 ፥ 1- 2

ፍላጎት አለ ፤ እቅድ አለ ፤ ውጥን አለ ። አገልግሎቱ ሰፍቷልና ስፍራ ጠባል ። ሰፊ ስፍራ አስፈላጊ ነውና ሰፊ ሃሳብ መጥቶአል ። ቤቱን እናስፋው ሌላ ቤት እንጨምር ግሩም ሃሳብ ፤ ግሩም እቅድ ፤ ግሩም እይታ ።

እነዚህ የነቢያት ልጆች ጥሩ ምሳሌዎቻችን ናቸውና አብረናቸው እንጓዝ ------

አካባቢያቸውን ያያሉ ----- የሕዝቡን ብዛት አስተዋሉ
መደረግ የሚገባውን ያስተውላሉና ------ ቤት እንጨምር አሉ
አድራጊዎች ናቸውና ------- ሄደን እንጨት እንቁረጥ አሉ

እርስዎ ! አካባቢዎን ያያሉ ?------- ነፍሳት መጨመራቸውን ያስተውላሉ ?

መደረግ የሚገባውን ያደርጋሉ ?-------- ለመስፋት ፤ ለመብዛት ፈቃደኛ ነዎት ? እቅድ ያወጣሉ ?

ለማስደረግ ጊዜ ይፈጃሉ ?-----ወይስ-----ያደርጋሉ ?

የነቢያት ልጆች ሃሳብ አመንጪዎች ብቻ ሳይሆኑ አድራጊዎችም ናቸውና ሰሩ ፤ በዙ --------- እርሶሳ ?

የእርስዎ ሃሳብ ፤ በእርስዎ ካልሆነ በማን ይሰራል ብለው ያስባሉ ?

እንየው ፤ እናስተውለው ፡ እኛው እናድርገው ።
ዘመን ! እየሮጠ ነውና

# ይቻላል !

ከእነርሱም አንዱ ምሰሶውን ሲቆርጥ የምሳሩ ብረት ወደ ውኃው ወደቀ እርሱም ፡- ጌታዬ ሆይ ፥ ወየው ! ወየው ! የተዋስሁት ነበር ብሎ ጮኸ ።

2 ነገ 6 ፥ 5

በዝተናል ፤ ስፍራ ጠቦናል ሲባል ተጨማሪ ስፍራን ለመስራት ሆ ! ብሎ ከወጣው ሕዝብ ጋር አብሮ ወጣ ።

ለማንም ምንም አላለም ፤ አለመቻሉን አላሳየም ፥ ነገር ግን አብሮ ለስራው ታደመ ፤ ወጣ ፤ ሄደ ።

አቅም ፤ ጉልበት የለኝም እቀራለሁ ብሎ ወደ ኋላ አላለም ነገር ግን ወጣና መጥረቢያ ተውሶ መጣ ፤ ሄደ ከህብረቱ ጋር የህብረቱን ስራ ለመስራት ፤

ላለማደግ ምክንያት እንዳይሆን ጣረ ፤ ለሕብረት እንቅፋት ላለመሆን ወሰነ ሄደ መጥረቢያ ተውሶ መጣ ። ከሕብረቱ ጋር ወጣ ፤ ሄደ አገለገለ ።

ምንም አላለ ፤ መዋሱን ለመናገርም አልጣረ ። ሄደ በስራው በረታ ።

ይቻላል ! ይህ ለትምሕርታችን ተፅፏልና ። አልችልም ፤ የለኝም ከማለት ፥ ከትልቁ ስራ ከመቅረት እንዲህም ይ-ቻ-ላ-ል-